Week 9

Grade 2

# ሀገር ስጪኝ



Leveled

# ሀገር ስጪኝ

Leveled | Grade 2 | Week 9



ይህ አጋዥ የንባብ መጽሐፍ ከዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲ. (USAID) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በሴቭ ዘ ቺልድረን (Save the Children)፣ በትምህርት ሚኒስቴር እና በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ የጋራ ትብብር ተዘጋጅቶ ታተመ::

2008 ዓ.ም.

The CC By license lets others distribute, adjust, and build upon this work, for free or commercially, as long as credit is given to the original creation. However, any changes from the original must be indicated.

For more info please refer: *https://creativecommons.org/licenses/*



ዙቤይዳና ዳንኤል እንቆቅልሽ
ይጠያየቃሉ::



“ዙቤይዳ በነጭ ወረቀት ላይ ዘሯን የምትዘራ?”



ዳንኤል “ይህማ ቀላል ነው ፤ እስክርቢቶ” በማለት መለሰላት።

ዙቤይዳ “እስኪ አንተ ደግሞ ጠይቀኝ”



ዳንኤል “ቢሄዱት ቢሄዱት የማያልቅ?”



ዙቤይዳ "መንገድ" በማለት መለሰች::




ዳንኤል "አይደለም፤ እንደገና ሞክሪ" አላት።



ዙቤይዳ “ወንዝ” አለች ፡፡
እየሳቀች፡




ዳንኤል “ተሳስተሻል፤ ሀገር ስጪኝ” አለ።



ዙቤይዳ “አንድ ዕድል ስጠኝ! አወቅሁት! ሰማይ ነው።”




ዳንኤል “በይ ሀገር ስጪኝ?”



ዙቤይዳ “ውዷን ኢትዮጵያን ሰጥቼሃለሁ።”




ዳንኤል "ኢትዮጵያ! ኢትዮጵያ ተቀምጬ ምን አጥቼ፤ ሁሉም በእጄ፤ መልሱ ሃሳብ ነው።"